የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Regional Integration

# የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር

# በውልና በኢንቨስትመንት እርሻ የለማ ምርት የግብይት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 929/2015

# በውልና በኢንቨስትመንት እርሻ የለማ የሰብል ምርት የግብይት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 929/2015

በውልና በኢንቨስትመንት እርሻ የለማ የሰብል ምርት የግብይት አሰራር ስርዓት በመዘርጋት የአምራቹን እና የአስመራቹን መብቶች እና ጥቅሞችን ማስከበር በማስፈለጉ፣

በውል እና በኢንቨስትመንት እርሻ የተመረቱ ምርቶች ግብይት ስርዓት ዉስጥ የሚታዩ ህገ-ወጥ ድርጊቶችን እና የሚቀርብ የተዛባ የምርት መረጃዎችን በመከላከል ፍትሃዊና በዉድድር ላይ ተመሰረተ ግብይት ስርዓትን በማሳለጥ የወጪ ምርቶች ለወጪ ገበያ በማቅረብ የገቢ ግኝትን ገቢ ማሳደግ በማስፈለጉ፣

የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ደንብ ቁጥር 377/2008 አንቀጽ 21 እና የሰሊጥ እና ነጭ ቦሎቄ ግብይት ደንብ ቁጥር 178/2002 አንቀጽ 27 መሰረት የንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “በውልና በኢንቨስትመንት እርሻ የለማ የሰብል ምርት ግብይት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 929/2015” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

1) **“የሰብል ምርት”** ማለት የጥራጥሬ ምርቶች እና የቅባት እህሎች ናቸው፤

2) **“የምርት ዘመን”** ማለት በኢትየጵያ ዘመን አቆጣጠር ከህዳር 1 ቀን ጀምሮ እስከ ሚቀጥለው ዓመት ጥቅምት 30 ድረስ ሆኖ በመስኖ የሚለማ ግን አምራቹ ምርቱ የሚደርስበትን ጊዜ ገልጾ የሚያስመዘግበውን የምርት ዘመን ነው ተብሎ ይወሰዳል፤

3) **“የጸና ውል”** ማለት የሰብል ምርቶች የሚመለከቱ ግዴታቸውን ለማቋቋም ወይም ለመለወጥ ወይም ለማስቀረት በአምራች እና በአስመራች መካከል የተገባ ውል ሆኖ ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ውል ነው፤

4) **“የሰብል ምርትን የማስመረት ውል”** ማለት በአስመራች እና በአምራች መካከል በሰብል ምርቶች ላይ የሚደረግ ውል ነው፤

5) **“የሰብል ምርትን በውል አስመራች”** ማለት የሰብል ምርትን ከአምራች ጋር ለማስመረት ውል የገባና ወደ ውጪ የሚልክ ማንኛውም ሰው ነው፤

6) **“የሰብል ምርትን በውል አምራች”** ማለት የሰብል ምርትን ከአስመራች ጋር ውል በመግባት የሚያመርት አርሶ አደር ነው፤

7) **“ባዕድ ነገሮች”** ማለት የምርት ጥራትን የሚያጓድሉ አፈር፣ ጠጠር፣ የነቀዘ፣ የሻገተና አላስፈላጊ የሰብል ዘር እና የመሳሰሉት የሚያጠቃልል ነዉ፤

8) **“በኢንቨስትመንት የለማ ሰብል”** ማለት አምራቹ በራሱ ማሳ ላይ የኢንቨስትመንት ፍቃድ አውጥቶ በኢንቨስትመንት የለማ የሰብል ምርት ነው፡

9) **“አግባብ ያለው ባለስልጣን”** ማለት የንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር እና በክልል የንግድ ሥራን ለማሰተዳደር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው፤

10) **“ሚኒስቴር”** ማለት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ነው፤

11)**“የበላይ አመራር”** ማለት የንግድና ቀጣናዊ ትስሰር ሚኒስትር ወይም የንግድ ትስሰር እና የወጪ ንግድ ፕሮሞሽን ዘርፍ ሚኒስትር ዲኤታ ማለት ነዉ፤

12) **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

13) ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአስገዳጅ ግብይት ሥርዓት ዉስጥ በሚያልፉና ለወጪ ገበያ በሚቀርቡ በኢንቨስትመንትና በውል እርሻ ለምተዉ ለግብይት በሚዉሉ የሰብል ምርቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለ ምዝገባ ሥርዓት</u>

4. **በውልና በኢንቨስትመንት እርሻ የለማ የሰብል ምርት መረጃን የማስመዝገብ ሥርዓት**

1) ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ በውል እርሻ የለማ የሰብል ምርት መረጃን ይመዘግባል፡-

ሀ) ሰነድን በሕግ ለማረጋገጥ ሥልጣን በተሰጠው አካል የጸደቀ በአምራችና አስመራች መካከል የተገባ የጸና ውል ሲቀርብ፣

ለ) በውል የለማ የሰብል ምርት ዓይነት፣ መጠን እና የመሬት ሽፋንን በየደረጃው ከሚገኙ የንግድ ሥራን ከሚያስተዳድሩ የክልል አካላት የተሰጠ የማረጋገጫ ሰነድ ሲቀርብ፣

ሐ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል (ለ) በተደነገገዉ መሠረት የተሰበሰበዉ የሰብል ምርት መጠን መረጃ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ለሚኒስቴሩ ሲቀርብ፤ እና

መ) አስመራቹ ያስመረተዉን ምርት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የምርት መረከቢያ ማዕከል አቅርቦ በትክክል የተመዘነ የምርት መጠንን መረጃ ማረጋገጫ ሰነድ ሲቀርብ፤ ናቸው፡፡

2) ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ በኢንቨስትመንት እርሻ የለማ የሰብል ምርት መረጃን ይመዘግባል፡-

ሀ) የኢንቨስትመንት የእርሻ መሬቱ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ እና የንግድ ሥራ ፈቃድ ሲቀርብ፣

ለ) በምርት ዘመኑ ያለማው የምርት ዓይነትና የመሬት ሽፋን በየደረጃው ከሚገኙ የንግድ ሥራን ከሚያስተዳድሩ የክልል አካላት የተሰጠ የማረጋገጫ ሰነድ ሲቀርብ፣

ሐ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ 2 ፊደል (ለ) በተደነገገዉ መሠረት የተሰበሰበዉ የሰብል ምርት መጠን መረጃ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ለሚኒስቴሩ ሲቀርብ፣ እና

መ) አልሚዉ ያመረተዉን ምርት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የምርት መረከቢያ ማዕከል አቅርቦ በትክክል የተመዘነ የምርት መጠን መረጃ ማረጋገጫ ሰነድ ሲቀርብ፣ ናቸው፡፡

5. በውልና በኢንቨስትመንት እርሻ የለማ ምርት ግብይት የአሠራር ሥርዓት

1) በውል እርሻ የለማ የሰብል ምርት ግብይት የአሠራር ሥርዓት የሚከተሉትን ጉዳዮች ያካትታል፡-

ሀ) በውልና በኢንቨስትመንት እርሻ የለማ ምርት ሻጭ በሆኑ አምራችና ገዢ በሆኑ አስመራች መካከል በተገባ ውል መሠረት ብቻ ግብይት መፈጸም፤

ለ) በትክክል እና በተጨባጭ በተመረተ የምርት መጠን መረጃ መሠረት ግብይት ማካሄድ፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ንዑስ ፊደል (ሀ) መሠረት የሚደረግ ግብይት የምርቱን ዓይነት፣ መጠን እና ጥራት ሳይጓደል ግብይት መፈጸም፤

መ) አምራችና አስመራች በገቡት ውል መሠረት ምርቱ ከተመረተ በኋላ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ግብይት ማካሄድና ክፍያውን በባንክ በኩል መፈጸም፤

ሠ) አስመራች ምርቱን እንደተረከበ በአካባቢው በሚገኝ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የምርት መረከቢያ ቅርንጫፍ ማዕከል በማቅረብ ማስመዘንና ትክክለኛ የምርቱን

መጠን መረጃ ማረጋገጥ፤

ቀ) በውል እርሻ የተመረተ የሰብል ምርት የተደነገጉ የግብይት ደንብና መመሪያዎች መሠረት የማጓጓዝና የማከማቸት አሠራር ሥርዓት በመከተል መፈጸም፤

ሰ) በውል እርሻ የለማ የሰብል ምርት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ምርቱን በማዘጋጀት ለውጪ ገበያ በማቅረብ ሽያጭ መፈጸም፤ ናቸው፡፡

2) በኢንቨስትመንት እርሻ የለማ የሰብል ምርት የግብይት የአሠራር ሥርዓት የሚከተሉትን ጉዳዮች ያካትታል፡-

ሀ) አልሚው በትክክለኛ ያመረተውን ምርት መጠንና ዓይነት በአካባባው በሚገኝ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የምርት መረከቢያ ማዕከል በማቅረብ ማስመዘንና ትክክለኛ የምርቱን መጠን ማረጋገጥ፤

ለ) አልሚው የተመዘነዉን ምርት መጠን መረጃ ለሚኒስቴሩ በአስራ አምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ መረጃዉን ማቅረብ፤

ሐ) በአልሚ የለማ የሰብል ምርት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ምርቱን በማዘጋጀት ለውጪ ገበያ በማቅረብ ሽያጭ መፈጸም፤

3) አስመራቹ ወይም አልሚው በውል ወይም በኢንቨስትመንት እርሻ ያለማውን የሰብል ምርት በበጀት ዓመቱ በማስመዝገብ ለገበያ ካላቀረበ በቀጣዩ የምርት ዘመን ማስመዝገብም ሆነ ወደ ውጪ መላክ አይችልም፡፡

## ክፍል ሶስት

## የአስመራች፣ አግባብ ያለው ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ተግባር እና ኃላፊነት

### 6. የአስመራች ተግባር እና ኃላፊነት

1) በውልና በኢንቨስትመንት እርሻ አስመራች፡-

ሀ) የገባውን የጸና ውል እስከ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ በሚኒስቴሩ ማስመዝገብ ይኖርበታል፤

ለ) ማንኛውም አስመራች ያስመረተውን ምርት በዓይነት፣ በመጠን እና በጥራት ብቻ በገባው ውል መሠረት ከአምራቹ ግዢ መፈጸም እና መረከብ አለበት፣

ሐ) አስመራች ያስመረተውን ምርት በምርት ዘመኑ እስከ ስድስት ወራት ባለዉ ጊዜ

ዉስጥ ብቻ ለገበያ አቅርቦ መሸጥ አለበት፤

መ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል (ሐ) መሠረት ሽያጭ መፈፀም ካልቻለ ሚኒስቴሩ ጋር ቀርቦ ምርቱን ለገበያ ማቅረብ ያልቻለበትን አሳማኝ ምክንያት በማስረዳት እና በማስመዝገብ እስከ ሶስት ወራት ጊዜ ድረስ እንዲራዘምለት መጠየቅ ይችላል፤

ሠ) አስመራች ያስመረተውን ምርት ካስመረተበት አካባቢ ወደ ምርት ገበያ ሲያጓጉዝ ግብይትን ለመምራት ሥልጣን ከተሰጠው አካል የመሸኛ ሰነድ በመያዝ ማጓጓዝ ይኖርበታል፤

ረ) አስመራች ከአምራቹ ላይ በትክክል የተረከበውን የምርት ዓይነት እና መጠን በክልል የንግድ ሥራን ለማስተዳዳር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል በወቅቱ ማቅረብ አለበት፤

ሰ) አስመራች ያስመረተውን ምርት በአካባቢው በሚገኝ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የምርት መረከቢያ ማዕከል በማቅረብ በማስመዘንና በማረጋገጥ መረጃ ማቅረብ አለበት፣

ሸ) አስመራች ያስመረተዉን የሰብል ምርት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ምርቱን በማዘጋጀት ለውጪ ገበያ በማቅረብ ሽያጭ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

2) በዚህ አንቀፅ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ተላልፎ የሚገኝ አስመራች በዚህ መመሪያ፤ ግብይትን በሚያስተዳድሩ ሕጎች፣ የንግድ ምዝገባ ፈቃድን በሚያስተዳድሩ ሕጎች ወይም እንደጉዳዩ አግባብ የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላል፡፡

## 7. አግባብ ያለው ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት

1) የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት፡-

ሀ) በውልና በኢንቨስትመንት እርሻ የለማ የሰብል ምርት መረጃ ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል እንዲሁም አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣

ለ) በውል እና ኢንቨስትመንት እርሻ የተመረተ ምርት የግብይት ሥርዓትን ያስተባብራል፤ አፈጻጸሙን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

ሐ) አምራቾችና አስመራቾች ያመረቱትን ወይም ያስመረቱትን ምርት ወደ ውጪ እንዲልኩ የወጪ ሽያጭ ውል ምዝገባ ያከናውናል፤ በተጨማሪም የምርት መላኪያ ይሁንታ አገልግሎት ይሰጣል፤

መ) በውል እና ኢንቨስትመንት እርሻ የተመረተ ምርት ግብይትን ለማሳለጥና

በትክክለኛ መረጃ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤

ሰ) በዚህ መመሪያ መሠረት የተደነገጉ ድንጋጌዎችን በማስፈጸምና የመረጃዎችን ትክክለኝነት በማረጋገጥ ግብይትን ለማሳለጥ እንዲቻል ልዩ ኮሚቴ ያቋቁማል፤

ረ) በዚህ መመሪያ ከተደነገገው ውጪ ጥያቄዎች ሲመጡ በማጣራትና በማረጋገጥ በበላይ አመራር ዉሳኔ እንዲያገኝ ይደረጋል፤

ሸ) የለሙ ምርቶችን መረጃ መሠረት በማድረግ በትክክለኛ ዋጋ ምርት ስለመገዛቱ ወይም በዓለም አቀፍ የመሸጫ ዋጋ የሎጂስቲክ ወጪን ታሳቢ በማድረግ ለወጪ ገበያ ስለመሸጡ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

ቀ) አምራቹ የተፈቀደለትን የምርት መጠን መረጃ መነሻ በማድረግ የኤክስፖርት ክምችት የምርት ሚዛን በመተንተን እና በማደራጀት ለወጪ ገበያ እንዲቀርብ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

በ) አምራች ላኪ ድርጅቶች ቅሬታ የሚያቀርቡበት የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ለቅሬታቸው ምላሽ ይሰጣል፤

ተ) የዚህን መመሪያ ተፈጻሚነት በመከታተል በመመሪያው መሠረት በማይሠሩ አካላት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

8. **የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ተግባር እና ኃላፊነት**

ሀ) በውል ወይም በኢንቨስትመንት የተመረቱ ምርቶችን በመመዘን ትክክለኛነታቸውን ያረጋግጣል፤

ለ) የሚቀርብለትን ምርት ሳይራገፍ ከነመኪናው በመመዘን የተጣራ የምርት ልኬት መረጃ ለአምራቹ ይሰጣል፤

ሐ) በውል ወይም በኢንቨስትመንት እርሻ የተመረቱ የሰብል ምርቶች አገልግሎቱን በሰጠበት ጊዜ የመዘናቸውን ምርቶችን መረጃ አደራጅቶ ለሚኒስቴሩ ያስተላልፋል፤

መ) ለመስኩ ጠቃሚ የሆኑ ከተግባር እና ኃላፊነቱ የሚመነጩ ሌሎች አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡

9. **የክልል ንግድ ሥራን ለማስተዳደር በሕግ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ) በውል ወይም በባለሃብቶች የሚለሙ የሰብል ምርቶችን መረጃዎችንና ማስረጃዎችን

ማሰባሰብ፣ መተንተን እና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚዘጋጅ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መረጃ ቋት ማስተላለፍ፤

ለ) በዚህ መመሪያ የሚሸፈኑ የሰብል ምርቶችን በማረጋገጥ ከማስረጃቸው ጋር የምርት የሽኝት ሰነድ መስጠት እና ወደ ተሸኙበት ቦታ ማጓጓዛቸውን ማረጋገጥ፤

ሐ) በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ በክልል የሰብል ምርትን ለማስተዳደር እና ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን ከተሠጣቸው አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት፤

መ) በዚህ መመሪያ የሚሸፈኑ የሰብል ምርቶች ሌሎች ጠቃሚ የሆኑ ተግባራትን ማከናወን፡፡

10. <u>የተከለከሉ ተግባራት</u>

1) ማንኛውም ኢንቨስተር ከራሱ ማሳ ካመረተው ወይም በውል እርሻ ካስመረተው ምርት ውጪ ለገበያ ማቅረብ፤

2) ማንኛውም ኢንቨስተር ከራሱ ማሳ ካስመረተው ወይም በውል እርሻ ካስመረተው ምርት ውጪ ማጓጓዝ ወይም ማከማቸት፤

3) በዚህ መመሪያ መሠረት የሚጓጓዙ የሰብል ምርቶችን ያለመሸኛ ማጓጓዝ፤

4) አግባብ ያለው ባለስልጣን እና ባለድርሻ አካለትን የሚያሳስት መረጃ ወይም ማስረጃ መስጠት፤

5) አስመራች ከአምራቹ የተረከበውን ምርት በአካባቢው ወደ ሚገኝ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ አቅርቦ መጠኑን ሳያረጋግጥ ለግብይት ማቅረብ፤

6) በውል ወይም በኢንቨስትመንት እርሻ የተመረቱ ምርቶችን በማስመዝገብ በበጀት ዓመቱ ያለማውጣት፤

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

11. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

12. <u>አስተዳደራዊ እርምጃ እና የቅሬታ አሰማም ሥነ-ሥርዓት</u>

1) አግባብ ያለው ባለስልጣን ይህንን በዚህ መመሪያ መሠረት በማይሠሩ ላይ እንደጉዳዩ አግባብ የንግድ ምዝገባና ፍቃድን በሚያስተዳድሩ ሕጎች ወይም ግብይትን በሚያስተዳድሩ ሕጎች

መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፤ ሕጋዊ እርምጃም ያስወስዳል፤

2) በዚህ መመሪያ መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ የተወሰደበት ማንኛውም ሰው ቅሬታ ካለው በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው ባለስልጣን የበላይ ኃላፊ ቅሬታውን በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፤

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) መሠረት ቅሬታ የቀረበለት የበላይ ኃላፊ በአስር ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡ ሆኖም የበላይ ኃላፊው በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ ወይም አስተዳዳራዊ ውሳኔውን ካጸናው፣ ቅሬታ አቅራቢው ጉዳዩን በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ አግባብነት ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

13. <u>ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ በተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራሮች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

14. <u>መመሪያውን ስለመሻር ወይም ስለማሻሻል</u>

ሚኒስቴሩ ይህንን መመሪያ መሻር ወይም ማሻሻል ይችላል፡፡

15. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከመስከረም 19 ቀን 2015 ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ገብረመስቀል ጫላ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚንስትር

**መስከረም 19 ቀን 2015 ዓ.ም**